በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ከኤፕሪል 1-10 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

ከኤፕሪል 11-20 እና ከኤፕሪል 21-30/2025 የሚኖረው የአየር

ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2025

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራቅ፣ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ አና በምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአርባምንጭ 29.3፣ በጎሬ 29.1፣ 10.3፣ ጅማ 13.2፣ መተሃራ 30፣ ነገሌ 12.4፣ ነቀምት 30.7፣ 20.6፣ 42.3፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 16.4፣ አይራ 21.2፣ አማን 16.6፣ 29.2፣ 25.4፣ አንግር ጉቲን 10.4፣ 16.2፣ 12.8፣ 21፣ አርጆ 20.6፣ 14.2፣ 18.6፣ 20.2፣ 21.5፣ 28.2፣ አሶሳ 20.5፣ 27.5፣ አይከል 10.9፣ 10.1፣ ሰቆጣ 14.5፣ በደሌ 19.8፣ 20.8፣ ቡለን 23.2፣ 46.4፣ ቡሬ 14.7፣ ቡርጂ 21.8፣ ጨዋቃ 37.6፣ ጭራ 30.3፣ 14፣ ደባርቅ 10.5፣ ደብረ ታቦር 12.8፣ ደምቢ ዶሎ 12፣ 17.5፣ 16.2፣ ዶሎ መና 10.7፣ ኢጃጂ 15.5፣ ጋቲራ 12.7፣ 29.3፣ 26.4፣ 10.4፣ ጊዳ አያና 25.9፣ 16.2፣ ቡሌ ሆራ 17፣ ጅንካ 11.8፣ 10.2፣ 14.3፣ 23.6፣ ላሊበላ 19.1፣ ላሬ 12፣ 12፣ ማጂ 55፣ ማንኩሽ 23፣ ምዕራብ አባያ 11፣ ነጆ 21.5፣ 31.8፣ ሳዉላ 23.5፣ ሻምቡ 26፣ ሽሬ 10.6፣ ወላይታ 15.5፣ ያቤሎ 37፣ ደንገጎ 13.3፣ ዶሎ ኦዶ 23፣ 19.8፣ ሂርና 11.4 እንዲሁም ኩርፋጨሌ 31.1 ሚሜ የሚደርስ ከመካለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ9 የሀገሪቱ አከባቢዋች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 37-55 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ37 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል በማጂ፣ በቡለን፣ በነቀምት፣ በጨዋቃ፣ በያቤሎ፣ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



ምስል፡1 ከኤፕሪል 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ ዞኖች ፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የመካካለኛዉ ጎንድር ዞኖች፣ የህርዳር፣ የአዊ ዞኖች፣የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ላይ ከ9-140 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ጎፋ እና የጋሞ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል አፍዴር፣ የዳዋ፣ ሊበን ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣ የህርዳር፣ የአዊ ዞኖች፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል በጋምቤላ፣ በመተማ፣ በፉኝዶ፣ በገዋኔ፣ በሰመራ፣ በአዋሽ አርባ፣ በጎዴ፣ በመተሃራ፣ በፓዌ፣ በጨዋቃ፣ በድሬ ደዋ፣ በአይሻ፣ በቀበሪዳህር፣ በአርባምንጭ፣ በኑራኤራ፣ በመኤሶ፣ በሸዋ ሮቢትና በቻግኒ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35.0 እስከ 43.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4) ፡፡



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን

1.2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በአብዛኛው የበልግ አብቃይና እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው ዝናብ ከነበረው የትነት መጠን አንጻር ሲተነተን በተለይም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለዉ ተዘርተው በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች እድገት እንዲሁም ለመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወን እና የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና ነበረው። በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እና ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው(ካርታ 5) ፡፡



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኤፕሪል የመጀመርያ አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው አባይ፣ እንዲሁም ተከዜ እና በመካከለኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ አባይ እና የላይኛው ባሮ አኮቦ በጣም ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የነበረው እርጥበትም ለገፀ ምድር ለውሃ ሀብት መጎልበት ጥሩ እንደነበር የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ በታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው በኦሞ ጊቤ፣ እና ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው እና ታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ከፊል ደረቅና ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ነበሩ (ካርታ 6) ፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2. መግቢያ

የበልግ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው በኤፕሪል የሚዘነበው ዝናብ ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ትግራይ፣ ምስራቅ አማራና ሱማሌ አካባቢዎችን ጨምሮ ከ70-120 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ10-20 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ማለትም የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ለ10 ቀናት ያህል እስከ 70 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ ክልል እና ደቡብ ኦሮሚያ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከ161-260 ሚ.ሜ ለ20 ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በተጨማሪም ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በኤፕሪል ወር በአብዛኛዉ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ40% እስከ 50% የሚደርስ የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ። በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በተሻለ መልኩ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ፡፡

2.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ እየተጠናከሩና እየተስፋፉ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ፡፡በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ጨምሮ የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8) ፡፡



ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20, የሚኖረወ የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር

<u>ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን</u>

ክልል	ዞን	የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን
አሮሚያ	ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣	መካከለኛ (እስከ 29 ሚ.ሜ)
	ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ መጠን እስከ ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ)
ሶማሌ	ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር. ነጎብ፣ ኤረር፣ ፋፈን፣ ሲቲ፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ጃራር እና ዶሎ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)

አማራ	የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የደቡብ ጎንደር፣ የአዊ የሰሜን ጎጃም፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
	የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የመካከለኛው ጎንደር ዞኖች፣	ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ)
ትግራይ	የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛው እና የምስራቅ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
	የምዕራብ እና የሰሜን መዕራብ	ቀላል መጠን
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	መካከለኛ መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ)
ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ጉራጌ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	አኙዋክ፣ መዥንግ እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ)
አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ		ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)

2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በበልግ ወቅት በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በኤፕሪል የሶስተኛው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ35 እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከ40 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 9) ።



ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

2.4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ በልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ እስከ አፕሪል የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን! በተጨማሪም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጋር ተያይዞ ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪዎቹ የኤፕሪል ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ ተጠቃሚ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 10)፡፡



ካርታ 10 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.5 እ.አ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እርጥበት ይኖራቸዋል። ይህም ሁኔታ ቀደም ብለው ለተዘሩ ለበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፣ እንዲሁም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንሰሳት መኖና ለመጠጥ ውሃ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ባጠቃላይ በቀጣይ አስር ቀናት ሊኖር የሚችለው የእርጥበት ሁኔታ ሊያሳድር የሚችው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲሁም የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከታች ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

ዞኖች	የእርጥበት ሁኔታ	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
የመኸር እርጥበት ተጠቃሚ ዞኖች				
ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን ጎጃም ዞኖች፣ ከትግራይ የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ዞኖች ፣አኝዋክ፣ መዠንግ እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት	• ለመኸር እርሻ ስራ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን • ለእንስሳት የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል • ለቋሚ ሰብሎች እድገት	• የትነት መጠን በአንዳንድ ቆላማ አካበቢዎች ሊጨምርና የአፈር ውስጥ እርጥበት ሊቀንስ ይችላል • ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት በሰብሎች እና በእጽዋት እድገት ላይ አሉታዊ ጎን ይኖረዋል	• ለመኸር እርሻ ለማሳ ዝግጅት የቅድመ ዝግጅት ማድረግ • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን • የእርጥበት
በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች				
የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ደቡብ ትግራይ፤ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ጉራጌ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ኤረር፣ ፋፈን፣ ሲቲ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ ምዕራብ ኦሞ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬደዋ ፣ ሐረሪ ኤረር፣ ፋፈን፣ ሲቲ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	• የማሳ ዝግጅት ለማድረግ • ዘር ለመዝራት • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት • ለሰብሎች እድገት የአፈር ውስጥ እርጥበት መጠን መሻሻል • የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም	• የሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት የአፈር መሸርሸር ሊያሰከትል ይችላል • በሰብል ማሳዎች ላይ የወኃ መተኛት ሊከሰት ይችላል • በአንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ትነት፣ የእርጥበት እጥረት እና ተከታይ ደረቅ ሰሞናት መኖር	• ዘር ለመዝራት የሚያስችል በቂ ዝግጅት ማድረግ • የእርጥበት መብዛት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች ከማሳ ውስጥ የውኃ ማንጣፈፍ ተግባራትን ማከናወን • የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን • የዳጋፌ መስኖ የዝናብ ውሃ ማሰባባሰብ • በሰብል ማሳ የውሃ መከተር ማከናወን

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች				
ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር. ነጎብ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	• የማሳ ዝግጅት ለማድረግ • ዘር ለመዝራት • ለእንስሳት መኖ ልማት • ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት	• ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት • የአፈር መሸርሸር	• በደጋማ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት • የመኖ ልማት ለማከናወን የግብዓት አቅርቦት ዝግጅት ማድረግ • የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን

2.6 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት የኤፕሪል ሁለተኛ አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ።ይህ ሁኔታ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰትንም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት ክምችትን ያሻሽላል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ንዑስ ተፋሰሶች በኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በከተሞችም ሆነ ረባዳማ በሆኑ የገጠር አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል ይህንነ አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ እና ለመከላከል እንዲሁም የሚገኘው ከፍተኛ እርጥበት በተገቢው ሁኔታ ለማከማቸት የሚያስችል የቅድመ ጥንቃቄና ዝግጅት ስራዎችን ከታች በተቀመጠው ምክር ሀሳብ መሰረት ማከናወን ያስፈልጋል።

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ

የውኃ ተፋሰሶች	የሚጠበቀው የእርጥበት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
አብዛኛው አሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ	ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት	• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል • የመጠጥ ወኃ አቅርቦተ መሻሻል • የመስኖ እና የሀይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ ከፍታ መሻሻል	• ቅፅበታዊ ጎረፍ • የውሃ በጎርፍና የውኃ ወለድ በሽታዎች ስጋት መጨመር • የደለል ወደ ግድቦች መግባት • የመሬት በጎርፌ መሸርሸርና መሰንጠቅ	• የፍሳሽ መውረጃዎች ማፅዳት • ያለውን የውሃ ሀበት ከብክለት መታደግ • የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም • የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችን ማከናወን • ውኃን ማሰባሰብ እና ማጠራቀም • ትንበያዎችን በቅርበት በመከታተል
በአብዛኛው አዋሽ፣ ዋቢ-ሸበሌ፣ ኦጋዴን ፣በመካከለኛ እና ታችኛው አባይ፣ የላይኛው ተከዜ	ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ እርጥበት	• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል	• ከፍተኛ ትነት • በቂ የውሃ ክምችት በሌለበት አካባቢ በተለይም አርብቶ አደር በእንስሳት በውሃ መጋጨት	• የዝናብ ውኃ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማሰባሰብ እና ማጠራቀም • የሚገኘውን የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር • በቆላማ አካባቢዎች የተጀመሩ ከቤት ጣራ ላይ የውኃ ማሰባባሰብ ተግባራትን አጠናክሮ ማከናወን
የአይሻ እና የመረብ ጋሽ ንዑስ ተፋሰሶች	ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ		• የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት መቀነስ • የውኃ ማጠራቀሚያዎች የውኃ መጠን መቀነስ • የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እጥረት	• የውኃ እጥረት ባለባቸው አካባቦዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ • የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር • የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም • የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et